

# የልዩ ትምህርት፣ ከቅድመ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል አጠቃላይ ግምገማ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች

ኦክቶበር 25፣ 2018

PCG Education

# አስፈላጊ ጥያቄዎች

1 የፕሮጀክት አቀራረብ እና የጊዜ ቅደም ተከተል እንዴት ነው?

2 ያሉት ጥንካሬዎች እና ለማሻሻል ያሉት እድሎች ምንድን ናቸው?

3 የሚቀርቡት የመፍትሔ ሃሳቦች ምንድን ናቸው?



# ፐብሊክ ኮንሰልታንሲ ግሩፕ (PCG) የትምህርት ቡድን

ዶ/ር ጄኒፈር ሚለር(Jennifer Meller)፡ ፕሮጀክት ዳይሬክተር

ዊሊ ጎዲሎ (Will Gordillo) ፡ የሙያ መስክ ኤክስፐርት

አና ዴንሪሞንት (Anna d'Entremont) ፡ የሙያ መስክ ኤክስፐርት

ዶ/ር ክሪስቲኒ ዶኒስ ኪሊር (Christine Donis-Keller) ፡ የግምገማ ባለሞያ

ማቲዉ ስኮት (Matthew Scott) ፡ የመረጃ ተንታኝ

PCG Education

# የሦስትዮሽ አቀራረብ




<u>የውጤት ትንተና</u>
- የተማሪዋቹ ብዛት እና የፕሮግራም ምደባ አዝማሚያዎቹ
- የተማሪ ውጤት አዝማሚያዋቹ

<u>ተቋማዊ እና ፕሮግራም ትንተና</u>
- ዳታ፣ ፖሊሲ እና አፈፃጸም ግምገማ
- የፕሮግራም ትንተና
- የሰራተኛ አመዳደብ ትንተና
- የገንዘብ ግምገማ

<u>የምርምር እና የአፈፃፀም ፅሑፎቹ</u>
- በወቅታዊ ፅሑፎቹ ላይ የተመሰረተ ግኝቶችና እና የመፍትሄ ሃሳቦች እና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪ ምርጥ አሰራር

# አቅጣጫ አመልካች ጥያቄዎች

የሚከተሉት ጥያቄዎች በኤሲፒኤስ (ACPS) ላይ ያደረግነውን ትንተና አቅጣጫ ያመለክታሉ፡፡

- በኤሲፒኤስ የሚሰጠው የትምህርት አገልግሎቶች  በትምህርት ቤት አስተዳዳር (ዲቪዥን) የሚገኙ የአካል ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች ፍላጎት ምን ያህል ያሟላል?
- የስቴት እና የፌደራል ደንቦችን በማስከበር  ረገድ የአካል ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ያላቸውን ፍላጎት የኤሲፒኤስ አገልግሎት ምን ያህል አሟልቶል?
- የአካል ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ለመደገፍ በቂ የሆኑ አገልግሎቶች ለመስጠት ኤሲፒኤስ ያለውን የሰው ሃይል ሃብት ምን ያህል ተጠቅሞል?
- የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎችን  ልዩ የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት የሚደረገውን የትምህርት ፕሮግራም  የሚደግፍ  የት/ ቤት እና የዲቪዥኑ ባህል የኤሲፒኤስ ትምህርት ቤት እና የአስተዳዳሩ(ዲቪዥኑ) አመራር ምን ያህል መፍጠር ችሎል?
- የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎችን በመደገፍ የኤሲፒኤስ የውስጥ እና የውጭ ግንኙነት ልምድ በሰራተኞች እና በቤተሰቦች መካከል ትብብር

# የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

| <u>የመመዘኛ መንገዶች</u> | ቃለመጠየቅ እና የተመረጡ የአትኩሮት ቡድኖች (2 ቀናት በመስክ) | መጠይቅ (2 መጠይቆች) ሰራተኞችና ወላጆች) | የፋይል ምርመራ (2 ቀናት) | መረጃ፣ ፖሊሲ እና የአፈፃፀም ግምገማ | ትምህርት ቤት ምልከታ እና ከተማሪው ጋር አብሮ ማሳለፍ (16 ቀናት በመስክ) |
|---|---|---|---|---|---|
| የትምህርት አሰጣጥ አገልግሎት | X | X | X | X | X |
| የስቴት እና የፌደራል መስፈርቶች | X | X | X | X | |
| የሰው ሃይል | X | | | X | X |
| የድጋፍ ባህልና ከባቢያዊ ሁኔታ | X | X | X | X | X |
| የግንኙነት ጥረቶች | X | X | X | X | |

# የጊዜ ቅደም ተከተል - የፕሮጀክት ደረጃዎች

## ደረጃ 1፡ የፕሮጀክት መጀመር (ጁን 2017)
- ፕሮጀክት ማስጀመር
- ፕሮጀክት እቅድ እና የጊዜ ቅደም ተከተል

## ደረጃ 2፡ የአቀራረብ ሂደቱን ማመቻቸት (ጁላይ - ኦገስት 2017)
- ስምምነት የተደረሰባቸው የውጤታማነት መመዘኛዋች
- የPCG ፕሮቶኮሎች፣ መሳሪያዋች፣ የመረጃ ጥያቄዋች፣ እና እንቅስቃሴዋች ውይይት
- ይፋ የመረጃዋች ጥያቄ ለዲስትሪክት ማቅረብ

## ደረጃ 3፡ መረጃ ማሰባሰብ እና መተንተን (ሴፕቴምበር 2017 - ማርች 2018)
- ባለድርሻዋችን ሥራ ማስጀመር
- የተገኙ መረጃዋች እና አርቲፋክትስ ማሰባሰብ
- የተመረጡ የጥናት ቡድኖች እና ቃለመጠይቆች ፤ የተማሪ ፋይል ምርመራ የተመረጠ የጥናት ቡድን
- የትምህርት ቤት ጉብኝት፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከተማሪ ጋር አብሮ መዋል

## ደረጃ 4፡ ጠቃሚ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት (ኤፕሪል - ኦገስት 2018)
- ትንተና ማካሄድ
- የፅሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት

## ደረጃ 5፡ ኮሚቴ እና ንዑሥ ኮሚቴ እና የስራ አተገባበር (ጁን - ኦክቶበር 2018)
- ከአንድ ሙሉ ቀን ስብሰባ በኋላ የዋና ኮሚቴ እና ንዑሥ ኮሚቴ ስራ ይቀጥላል።
- ለትምህርት ቤር ቦርድ እና ለሌሎች ባለድርሻዋች ማቅረብ
- ኤ ሲ ፒ ኤስ የስትራቴጂክ መርህ በመከተል የተግባር ፕላን ማዘጋጀትና የማጣራት ስራ ማከናወን

## ደረጃ 6፡ የድጋፍ ማጥራት ( 2018-19 የትምህርት ዘመን)

- PCG የ3-5 ዓመታዊ የተግባር እቅድ፣ የሚታየውን ልዩነት ትንተና፣ የአፈፃፀም መመሪያዋች ይመረምራል።

# ጥንካሬዎች እና የማሻሻያ እድሎች

# ጥንካሬ እና የማሻሻያ እድሎች

| ምእራፍ | ጥንካሬ | የማሻሻያ እድሎች |
|---|---|---|
| **II.** ህግ ማክበር (ኮምፕሊያንስ ) እና ተጠያቂነት | • አሳታፊ አቀራረብ ሁኔታ<br>• የተለይ አቀራረብ ሁኔታ<br>• የሚያቆርጥ እና የተመራቂ መጠን | • ተፈላጊ እርዳታ ውሳኔ<br>• ጎልቶ የሚታይ ሚዛናዊነት የጎደለው<br>• የውጤት ልዩነት |
| **III.** ባለብዙ ደረጃ የድጋፍ ሥርዓት | • ኤሲፒኤስ MTSS 2015 ማእቀፍ<br>• ከየዲፓርትሜንት የተውጣጣ አመራር<br>• የቴክኒዋሎጂ አጠቃቀም | • የትምህርት ቤት ልዩነቶች<br>• ዩኒቨርሳል ትምህርት ዲዘይን(UDL) |

# ጥንካሬዎች እና ለማሻሻል እድሎች

| ምእራፍ | ጥንካሬዎች | ለማሻሻል እድሎች |
|---|---|---|
| **IV.** ለአገልግሎት ማጨት እና ብቁነት | • የወላጅ ትብብር<br>• የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ(EL) መመሪያ | • ቅድመ ጣልቃ ገብነት/ልጅ ማፈላለግ ጥረት<br>• የባህል ብዝሃነት ድጋፍ |
| **V.** ማስተማር፣ መማር፣ እና የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ማህበራዊ የስሜት ድጋፍ | • በጋራ  ማስተማር<br>• ጣልቃ መግባት<br>• ከተማ አቀፍ ክፍሎች<br>• አጋዥ ቴክኒዎሎጂ | • የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕቲሚዝም) እና ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅ<br>• በጋራ  ማስተማር<br>• በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት አሰጣጥ |

# ጥንካሬዎች እና ለማሻሻል እድሎች

| ምእራፍ | ጥንካሬዎች | ለማሻሻል እድሎች |
|---|---|---|
| **VI.** የመማር እና የማስተማር ድጋፍ | • አስተዳዳራዊ ስብሰባዎች<br>• የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና | • በቦታው ላይ ያለ አመራረር<br>• የዲፓርትሜንት የጋራ ትብብር<br>• የሰራተኛ አያያዝ |
| **VII.** ትብብር፣ ግንኙነት እና የወላጅ ትብብር | • የወላጅ ተሳትፎ<br>• የወላጅ ትብብር<br>• የወላጅ ሪሶርስ ማዕከል | • ፍትሐዊነት<br>• የወላጅ ግንኙነት<br>• የለውጥ ማስመዝገብ |

# የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች

# የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች ምድቦች

1. ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS)
2. ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ማጨት፣ ምዘና እና ብቁነት አሰራር
3. የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕቲሚይዝም)፣ ጥብቅ አሰራር እና ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅ
4. አሳታፊ አሰራሮች
5. በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት አሰጣጥ እና የታለመ ጣልቃገብነት
6. አመራር እና ተጠያቂነት
7. በዲፖርትሜንት ውስጥ ያለ ትብብር
8. የሰራተኛ ምልመላ፣ አያያዝ እና ሞራል
9. ፋይናንስ
10. ባህል፣ ፍትሀዊነት እና የወላጅ ትብብር

# 1 ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS)

| | |
|---|---|
| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | - በMTSS ሂደት እና የሥርዓተ ትምህርት ማእቀፍ ላይ ተመስርቶ ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ዩኒቨርሳል ዲዛይን ያካተተ  አንድ ወጥነት ያለው እና ግልፅ መዋቅር ለአካዳሚክ ውጤት ፣ መልካም ባህሪ እና ማህበራዊ/ስሜት ትምህርት ማስተማሪያ ማዘጋጀት/ በስራ ማዋል።<br><br>- በትምህርት አስተዳደር(ዲቪዝን) እና በትምህርት ቤት ደረጃ ሥልጠናዎች እና የአቅም ግንባታ ላይ በቀጣይ በማካሄድ የስራ አፈፃፀም ብቃትን ማሳደግ እና ማሻሻል። |

# 1 ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS)

## እርምጃዎች ደረጃዎች

**የትምህርት አሰጣጥ**

- ዋነኛ የትምህርት አሰጣጥ ማጠናከር
- የትምህርት ዩኒቨርሳል ዲዛይን  ማስፈፀም
- የለውጦች እና የችግር ማስወገጃ የአሰራር ሂደቶች ባህላዊ ትርጎሜ ማገናዘብ

**አመራር**

- የMTSS ዘርፈብዙ ሙያ የዲሲፕሊን አመራር ቡድን መልሶ ማደራጀት
- በኤሲፒኤስ MTSS 2015 በተለይ የተቀመጡ አሰራሮችን የሚመለከት መመሪያ መስጠት

**የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና**

- የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እቅዶች፣ የሥልጠና አካላት እና የማቅረቢያ መንገዶች

**ተጠያቂነት**

- SST ሂደት መከታተል፤ የMTSS ምርጥ አሰራሮችን በስራ ማዋል
- ለስብሰባ፣ ለችግር መፍትሄ ለመፈለግ፣ ለውጥ ለመገምገም መረጃ መከታተል እና ጣልቃ መግባትን የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት

# 2 ለልዩ ትምህርት ማጨት፣ ግምገማ እና ብቁነት አሰራሮች

| | |
|---|---|
| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | - ትርጉም ያለው ስትራቴጂ በማዘጋጀት ለውጥ ለማምጣት ለልዩ ትምህርት ማጨት፣ ግምገማ እና ብቁነት አሰራር ለመተንተን የሚረዳ የመረጃ ትንተና ሲስተም ሂደት ማዘጋጀት፡፡<br><br>- በጊዜ ለውጥ የሚታየውን የመረጃ ለውጥ አዝማሚያ መከታተል ተደጋገሚ የሚታዩ ባህሪዎቸን (ፖተርን) ለመለየት እና እነዚህን መረጃ በመጠቀም የለውጥ ስትራቴጂዎቸን፣ እና ወጥነትን እና የአሰራር ተገቢነት ማሳወቅ (በተለይ በአስጊ አካባቢዎቸ የሚገኙ ተማሪዎቸን ከሚገባው በላይ ለይቶ የማውጣትን ቸግር ለማስቀረት፡፡) |

# 2 ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ማጨት፣ ግምገማ እና ብቁነት አሰራር

## የእርምጃዋች ደረጃ

**ቅድመ ሕፃናት**
- ስለEI እና ECSE ህዝብ ግንዛቤ እንዲያድግ መቀጠል
- ፍትሐዊነት፣ አክሰስ እና ዝውውርን ለማጠናከር አሁን በስራ ላይ ያሉ የመለያ አሰራሮችን መመርመር

**የልዩ ትምህርት**
- የአጠቃላይ ትምህርት ጣልቃ መግባት በትክክል በስራ ማዋል
- የእጪነት፣ ብቁነት እና ምደባ መረጃዋቾ በትምህርት ቤት ደረጃ መገምገም

**የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዋቾ**
- የኢ ኤል(EL) እና ኦ ኤስ አይ(OSI) ዲፖርትሜንቶቾ ኮሚቴ እንደገና ማዋቀር
- ኢ ኤል(EL) የሆኑ የSWDs ወላጆቾ ተሳታፊ የሚሆኑባቸውን ምርጥ አሰራር በስራ ማዋል

**ክፍል 504**
- የ504 መመሪያ መጽሐፍት በየዓመቱ ወቅታዊ ማድረግ፣ ሁሉንም አስፈፃሚ አካላት ማሰልጠን
- የክፍል 504 እቅዶቾ በትክክል በስራ መዋላቸውን ማረጋገጥ

# 3 የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕትሚዝም)፣ ጥብቅ አሰራር እና ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅ

**የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች**

- ለሁሉም ተማሪዎች የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕትሚዝም) እና ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅን የሚያሳይ ሁሉን ሥርዓት አቀፍ የሆነ ባህል መገንባት

- የማስተማሪያ ፕሮግራም በተመለከተ የማያቋርጥ ከፍ ያለ ውጤት በመፍጠር የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች እስከተቻለ ድረስ የለውጥ እመርታ እንዲያሳዩ፣ በአጠቃላይ የሥርዓት ትምህርት፣ ደረጃውን የጠበቀ የጠነከረ ትምህርት መስጠት እና ከፍተኛ ጥራት ያለው የጣልቃ ገብነት ስራ ማከናወን፣ የመለየት፣ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ማሻሻል እና በየክፍሉ በተለይ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ፕሮግራም መዘጋጀቱን ማረጋገጥ የልዩ ትምህርት ኢንስትራክሽን ቢሮ ዋነኛ አትኩሮት እንዲሆን ለትምህርት ቤቶች፣ ለብዙሃኑ ማህበረሰብ እንዲያውቅ ማድረግ።

# 3 የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕቲሚዝም)፣ ጥብቅ አሰራር እና ከፍ ያለ ውጤት መጠበቅ

## አርምጃዋች ደረጃ

**አወቃቀር እና የአሰራር ሂደቶች**

- የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕትሚዝም) መሆኑን አትኩሮት መግለፅ
- የተቀባይነት መንፈስ፣ ከፍ ያለ ውጤትን እንዲኖር ማበረታታት
- የአስተማሪዋችን ትብብር፣ የእቅድ ዝግጅት እና የሙያ ማጠናከሪያ ሥልጠና የሚያግዝ ዋና መርሃ ግብር እንዲኖር ማድረግ

**ጥብቅ አሰራር**

- በመረጃ ላይ የተመሰረተ አሰራሮች በተግባር ማዋል
- እንዴት ተማሪዋችን ማበረታታት፣ ከፍ ያለ የውጤት ደረጃ መጠበቅ፣ ልዩነት እንዴት መመልከት እና የትምህርት ግንዛቤ እንዴት ማሳየት እንደሚቻል የሙያ ማጠናከሪያ ሥልጠና ማካሄድ

**ተጠያቂነት**

- የአስተማሪዋችን የትምህርት አሰጣጥ እምነት ለመመዘን ዓመታዊ መጠየቅ ማካሄድ፣ እንደየስራ ድርሻው መተንተን
- የአካዳሚ ብሩህ ተስፋ (ኦፕትሚዝም)፣ ጥብቅ አሰራር እና ከፍ ያለ ውጤትን ለመፍጠር ከርእሰ መምህሮች ምን እንደሚጠበቅ ማስቀመጥ

# 4 አሳታፊ አሰራሮች

የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች

- ኤ ሲ ፒ ኤስ ለአብሮ የማስተማር አሰራር ያለውን ዝግጁነት ላይ ተመስርቶ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በመስጠት እና የትብብር ስራዎችን በማጠናከር እንዲሁም ከፍተኛ ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል አብሮ የማስተማር ሞዴል በስራ ማዋል፡፡

- በትምህርት ቤት ደረጃ የጊዜ ሰሌዳ አወጣጥ ስትራቴጂዎች፣ የአስተማሪ ቡድኖችን ጥራት ያለው እና ወጥነት ያለው አሰራር ለመቆጣጠር እና ለመገምገም እንዲሁም ከፍ ያለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል የአብሮ ማስተማር አሰራር ተቆማዊ ማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እና አሰራሮችን መፍጠር

# 4 አሳታፊ አሰራሮች

## የእርምጃዋች ደረጃ

**አወቃቀር እና የአሰራር ሂደቶች**

- የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት መመሪያዋች የሚመለከቱ ስልጠናዋች ማዘጋጀት እና መስጠት
- በጋራ ማስተማር ቡድኖች መቼ፣ የት እና በጋራ ቢያንስ ሊሰሩበት የሚገባውን የጊዜ መጠን የሚመለከት መመሪያ መስጠት

**በጋራ ማስተማር ቡድኖች**

- ውጤታማ በጋራ ማስተማር ቡድኖች መፍጠር
- በጋራ ማስተማር ቡድኖች ከዓመት ወደ ዓመት አብረው እንዲሰሩ የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት
- በየዓመቱ በጋራ ማስተማር ቡድኖች ግምገማ ማከናወን

**የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና**

- ወጥነት ያለው የማይቋረጥ ቀጣይ የግዴታ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መስጠት

**ተጠያቂነት**

- የፅሁፍ መመሪያዋች አፈፃፀም ትክክለኛነት መከታተል
- የተጠያቂነት የመዋቅር አሰራር መገንባት
- የውጤታማነት መለኪያ ማዘጋጀት

# 5 በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት አሰጣጥ (SDI) እና ዒላማ ላይ ያተኮረ ጣልቃገብነት

| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | |
|---|---|
| | - የተለየዩ አሃዛዊ የመጠን እና ጥራት መመዘኛ መረጃዋች መጠቀም ጣልቃገብነትን እና *(SDI)* በትክክል በስራ እየዋለ ስለመሆኑ መወሰን እና እነዚህን መረጃዋች በመጠቀም የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዋች በመላ የትምህርት አስተዳደሩ(ዲቪዝን) ደረጃ ውጤታቸው ፣ ማህበራዊ እና የስሜት ለውጦች እና የመልካም ባህሪ አሁን ባለው የ*SDI* እና የጣልቃ ገብነት የቅንጅት አሰራር መሰረት ምን ያህል እያደገ የመጣ ስለመሆኑ መረዳት<br><br>- ለእያንዳንዱ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ የተዘጋጀው ዒላማ ላይ ያተኮረ ጣልቃገብነት እና የ***SDI*** አፈፃፀም እና ውጤታማነት ትክክለኛነት መረጃ በመተንተን መገምገም<br><br>- ለአስተማሪዋችና ለ*IEP* ቡድን ቀጣይነት ያለው ሥልጠና መስጠት የ*IEP* ግቦችን በማሳካት የሚታዩ ለውጦችን ለማወቅ የሚያስችል ተገቢው መሳሪያ እነርሱ እንዲኖራቸው ማስቻል<br><br>- የተለመዱ መረጃዋች አሰባሰብ፣ የመፍትሄ የማፈላለግ እና የትምህርት አሰጣጥ እንደአስፈላጊነቱ መቀየር የተማሪዋችን ውጤት እና የማህበራዊ / የስሜት እድገት ለመደገፍ የሚከናውኑ ተግባራትን ደረጃ መጠን ለመወሰን የሚያግዙ ስለመሆናቸው አሁን በስራ ላይ ያሉ መመሪያዋችን እና መሳሪያዋችን መገምገም |

# 5 በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት አሰጣጥ (SDI) እና ዲላማ ላይ ያተኮረ ጣልቃገብነት

## የእርምጃዎች ደረጃ

**የትምህርት አሰጣጥ**

- የSDI አሰጣጥ አቅጣጫ አመልካቾ የስልጠና፣ ድጋፍ እና ሪሶዋርስ አቅርቦት የበለጠ አትኩሮት መስጠት
- አብሮ አስተማሪዎቾ እንዴት ትምህርቱን እንደሚያዘጋጁ፣ እንደሚያቅዱ፣ በስራ እንደሚያውሉ እና እንደሚገመግሙ ሥልጠና መስጠት

**ግንኙነት**

- የSDI ለውጥ እድገት ለወላጆቾ የሚገለፅበትን መመሪያ ማዘጋጀት
- የIEP ቡድን የሚታዩ ለውጦቾን እንዲከታተሉ መጠይቅ

**የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና**

- በIEP ሥልጠና የSDI ያለውን ተፈላጊነት ስፍራ ከፍ ማድረግ

**ተጠያቂነት**

- SDI አቅጣጫ አመልካቾ ማሳደግ
- የSDI እና በጋራ ማስተማር ደረጃ በደረጃ አጠቃቀም የሚያሳዩ መሳሪያዎቾን በመጠቀም ውጤታማ የሆነ መለኪያዎቾን ማዘጋጀት

# 6 አመራር እና ተጠያቂነት

| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | - በዓለም የታወቀ ትምህርት ለሁሉም ተማሪዎች ለማቅረብ የሚያስችል ትምህርት ለመቅረጽ ኤሲፒኤስ እንዴት የትምህርት ቤት እና የማእከላዊ ጽ/ቤት የስራ ኋላፊዎችን ተጠያቂነት አሰራር የሚያሳይ የተለያየ ገፅታ ያለው የተግባር እቅድ መፍጠር<br><br>- ቀጣይነት ያለው ለውጥ እና ፈጠራ ከማበረታታት በተጨማሪ ለመልካም የባህሪ፣ የአሰራር እና የባህል ለውጥ ለማምጣት የሚረዳ ዋና ስትራቴጂዎችን ለመመዘን የሚያስችል እርምጃዎችን መፍጠር |
|---|---|

# 6 አመራር እና ተጠያቂነት

## የእርምጃዎች ደረጃ

**አወቃቀር እና የአሰራር ሂደቶች**

- ልዩ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ትምህርት ለመደገፍ የማእከላዊ ጽ/ቤት ድርሻ ምን እንደሆነ ግልፅ ማድረግ
- በትምህርት ቤት ደረጃ "ለድርድር የማይቀርቡ" ጉዳዮችንና ከዋና ድ/ቤት የሚገኙ ድጋፎችን ለይቶ ማስቀመጥ

**ልዩ ትምህርት ማንዋል**

- አሁን ያሉትን መመሪያዎች በኢንተርኔት ላይ የመረጃ ልውውጥ (ኢንተራክቲቭ) የሚገኝበትን ሁኔታ ማዘጋጀት
- ከባለድርሻዎች ጋር በመተባበር የሚዘጋጀውን ማንዋል ለተጠቃሚ ምቹ እና ግልፅ እንዲሆን ማድረግ፡፡

**ተጠያቂነት**

- የልዩ ትምህርት የሚጠበቁ የውጤት ደረጃዎችን መመስረት
- የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን መምራት እንዲችል የልዩ ትምህርት የስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ተገቢውን ስልጣን መስጠት

# 7 በዲፓርትሜንቶች መካከል ትብብር

የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች

- የጋራ ሃብት ሪሶዋርስ እና የትምህርት ቤቶች ድጋፍ በአግባብ ለመጠቀም በ***OSI*** እና በሌሎች ዲፓርትሜንቶች ትብብር ማጠናከር በተለይም፤ *1)*የሰው ሃይል፤ *2)* የተማሪዎች አገልግሎት፤ አማራጭ ፕሮግራም ፤ *3)* የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አሰጣጥ እና ፤ *4)* የእንግሊዘኛ ቋንቋ አገልግሎቶች

- የተለያየ ዘርፍ የያዘ ቋሚ የስራ ቡድን መመስረት በቋሚነት በመገናኘት በጋራ የዲቪዝኑን የአሰራር ሂደት ለመመልከት እና በተግባር ውጤት ለማስመዝገብ

# 7 በዲፓርትሜንቶች መካከል ትብብር

## የሚወሰዱ እርምጃዎች

**በጋራ እንቅስቃሴ**

- በOSI እና በሰው ሃይል( HR) ፣ የተማሪዎች አገልግሎት፣ በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አሰጣጥ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) አገልግሎቶች በጋራ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን መለየት
- የእያንዳንዱን ትብብርና የኋላፊነት ድርሻ መመስረት፣ ያሉ ሃብቶችን  በጋራ ለመጠቀም ማመቻቸት

**የጋር ውሳኔ አሰጣጥ**

- ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ወጥነት ፣ ትብብር፣ እና የተቀናጀ አሰራር
- መረጃ ለመለዋወጥ፣ ችግሮችን ለመፍታት እና መፍትሔ ለማግኘት የተለመዱ፣ የትብብር ስብሰባዎች የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት

**ተጠያቂነት**

- ከሌሎች ዲፓርትሜንቶች ጋር በጋር የሚዘጋጁ ግቦች ሁሉንም በጋራ መወሰን
- የእድገት ለውጦችን ለመመዘን KPIs መወሰን

# 8 የሰራተኛ ምልመላ፣ አያያዝ እና ሞራል

የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች

- የትምህርት አስተዳደር ዲቪዝኑን የሰው ሃይል ሥርዓት ማሻሻል፤
  - በቅጥር ማመልከቻ እና የምርጫ ሂደት መለኪያ መስፈርት በማዘጋጀት ጭምር ዓላማ ያለው ምልመላ ለማካሄድ ብዙ ጊዜ እና ሃብት ሪስዋርስ መመደብ፣
  - ለአዳዲስ አስተማሪዋቸና ተዘማጅነት ያላቸውን አገልግሎት ለሚሰጡ እና መለስተኛ ባለሞያተኞች እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ እና ቀስ በቀስ ከፍ ያለ ኋላፊነት እንዲወስዱ እድል መፍጠር፣
  - ለአዳዲስ ሰራተኞች እድል እና ለለውጥ ተገቢ ጊዜ መስጠት፣እና፣
  - ቀጣይ የሆነ እድገት ለመፍጠር የሚረዳ ፕሮፌሽናል የመማሪያ ሥርዓት መፍጠር

# 8. የሰራተኛ ምልመላ፣ አያያዝ እና ሞራል

## የእርምጃዎች ደረጃ

**የሰራተኛ ምልመላ**

- የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች በይበልጥ ወደ ሚፈለጉባቸው ትምህርት ቤቶች ለመሳብ ማበረታቻ መፍጠር፣
- በተለይ ከፍተኛ እጥረት በሚታይባቸው የሞያ መስኮች በትምህርት አስተዳደር ዲቪዥኑን ውስጥ አማራጭ የሰርተፍኬት ማግኛ ፕሮግራሞች ቀጣይ ድጋፍ ማድረግ፣
- ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ትብብር መፍጠር፡፡

**ሰራተኛ አያያዝ**

- የልዩ ትምህርት አስተማሪ፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎችና መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች የስራ ዘመን ቆይታ ለማራዘም የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት
- በየሩብ ዓመት ያለው የሰው ኃይል/ መረጃ ክትትል ማድረግ
- የሰራተኞች የተመረጠ ቡድን መምረጥ ሰራተኞች የሚገጥማቸው ፈተናዎች ይበልጥ መረዳት

**ሥልጠና እና ድጋፍ**

- ከስራ ጋር የተጣመረ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና በመስጠት የሰራተኞችን እውቀት ማሳደግ፣
- ከልዩ ትምህርት ውጭ የሆኑ አስተማሪዎች የልዩ ትምህርት ሰርትፍኬት እንዲያገኙ ማበረታቻ መስጠት፣
- በተግባራዊ ስራ በራሳቸው መተማመን እንዲያዳብሩ አዲስ ለማጅ ሰራተኞችን ከፍተኛ ተፈላጊነት ባላቸው ትምህርት ቤቶች መመደብ

# 9 ዱይናንስ

| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | - የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎችን የሚደግፉ ሰራተኞች በቂ ቁጥር መኖራቸውን  እና የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟላ በቂ ሃብት ሪሶዋርስ መኖሩን ለማረጋገጥ የሰራተኞችን ምደባ ማጥናት<br><br>- ለልዩ ትምህርት ተፈላጊው የገንዘብ በጀት እና የማእከላዊ ድ/ቤት የሚከተሉትን ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>▪ የተማሪውን ፍላጎት አንገብጋቢነት መጠን እና የሚፈልገውን የድጋፍ አገልግሎት ዓይነት፣<br>▪ የተሟላ ቀጣይ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል በስራ ማዋል፣<br>▪ በትምህርት ቤት ውስጥ ላሉ ሰራተኞች የሚፈለጉ ድጋፍ ሥልጠና መስጠት፣<br>▪ የልዩ ትምህርት ሕግ መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ። |
|---|---|

# 9 ፋይናንስ
## የእርምጃዎች ደረጃ

**ምደባ**

- የሰራተኞች ምደባ ጥልቀት ያለው ትንተና አካሂድ
- ተዛማጅ አገልግሎት ለሚሰጡ የሚመደበውን የስራ መጠን ተመጣጣኝ ማድረግ፣

**ቅልጥፍና**

- በምደባ፣ በቁጥጥር እና የስራ ምደባ በማመጣጠን  ያለው ሃብት በተሻለ ለመጠቀም በት/ቤት ያለውን የሰው ሃይል ሃብት በሚገባ መጠቀም

**CCEIS**

- አስቀደሞ ጣልቃ ለመግባት የተቀናጀ አገልግሎት (CCEIS) የገንዘብ (ፈንድ) እቅድ በጋራ መመስረት፣

**ወጪ የሚያስወጡ ጉዳዮች**

- ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትሉትን እና የወጪውን አካሄድ ለመከታተል የሚያስችል ደረጃ ማውጣት፣
- የወጪ አካሄድ የሚያሳይ አንድ ወጥ የሆነ ሪፖርት ማዘጋጀት

# 10 ባህል፣ ፍትሀዊነት እና የወላጅ ትብብር

| የመፍትሄ ሃሳብ ምክሮች | |
|---|---|
| | - በትምህርት ላይ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ለሁሉም ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሥርዓት በመለየት መስጠት<br>- በት/ቤት እና በመኖሪያ ቤት ያለው ግንኙነት በማጠናከር በባህል እና በቋንቋ የተለዩ ወላጆች የልጆቻቸውን ትምህርት እንዲያግዙ እና በሁሉም የኤሲፒኤስ የትምህርት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እኩል የሆነ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማገዝ፣<br>- ሞቅ ያለ፣ ክብር የሚሰጥ እና የሚጋብዝ እንዲሁም የተለያየ የቤተሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ተለዋዋጭ ሁኔታ በመፍጠር የወላጆች እና የማህበረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ<br>- ጥንካሬ በብዝሃነት ለሚለው ምላሺ መስጠት የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች እና ሌሎች በቂ ድጋፍ የማያገኙ፣ ለአደጋ የተጋለጡ እና የኢኮኖሚ ዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን ውጤታማ የሆነ የማካተት እና የማዋሃድ የሚያስችል ባህል መፍጠር |

# 10 ባህል፣ ፍትሐዊነት እና የወላጅ ትብብር

## የእርምጃዎች ደረጃ

**እይታ**

- ለቤተሰብ ተሳትፎ ስለሚኖር እይታ የሚገልፅ መግለጫ አዘጋጅ
- ስለ ቤተሰብ ትብብር መሰረታዊ እምነቶችን ተወያይ

**ትብብር የሚያመቻች ቡድን**

- የልዩ ትምህርት የቤተሰብ ተሳትፎ የዲቪዝን ቡድን አደራጅ
- የተማሪዎችን የመማር እና የመተማመን ግንኙነት አጠናክር

**ተጠያቂነት**

- የቤተሰብ ትብብር እንቅስቃሴዎችን የስራ አፈፃፀም እና ውጤትን ገምግም
- የተግባር እቅዶች በየዓመቱ ገምግም

# ከዲቪዥን የሚፈለጉ ቁርጠኝነት

- የተለያዩ የትምህርት ቤቶች ስብስብ ሥርዓት ከመሆን ይልቅ እንደ አንድ ዓይነት የትምህርት ሥርዓት ለመስራት መወሰን
- ውጤትን ለመመዘን የሚያስችል ዋና ክንውን አመልካቾ (KPIs) ማዘጋጀት
- የሃብት አጠቃቀም (የገንዘብ፣ የሰው ሃይል)
- ከስትራቴጂ እቅድ ጋር የሚጣመር የተግባር ፕላን እንቅስቃሴዋችን ማቀናጀት
- ለሕዝብ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት እና ተሳትፎ ትብብር
- የቀረቡ የመፍትሄ ሃሳቦችን በስራ ለማዋል 3-5 ዓመታት ያለማመንታት ለማከናወን መወሰን

# ስኬቶችን መለኪያ ምሳሌዎች

- በ SPP የሚታዩ መስፈርቶችን ማሟላት
- ከስቴት አማካኝ ዝቅ ያለ የተለየ ሁኔታ በተለይ ለአፍሪካ አሜሪካውያን ተማሪዎች
- ከቨርጂኒያ ትምህርት ዲፓርሜንት(VDOE) ብዙ የተለየ ያልሆነ ፡፡ በፈቃደኝነት(ግዴታ የሌለበት) አስቀደሞ ጣልቃ ለመግባት የተቀናጀ አገልግሎት (CCEIS) ለመከላከል የሚውል የገንዘብ ምደባ
- በተለይ በከፍተኛ የትምህርት ክፍሎች የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ደረጃ መመዘኛ (SOLs) የተፋጠነ የብቃት አቅጣጫ ለውጥ
- በሰራተኞች መጠይቅ መረጃ ነጥቦች የታዩ ለውጦች፤ ለምሳሌ ፣
  - የ MTSS ማእቀፍ በትክክል ትምህርት ቤታቸው እየተጠቀመ መሆኑን የሚስማሙት ብዛት(የመነሻ አሃዝ በመቶኛ 73%) እየጨመረ መምጣት
  - የIEP ግቦችን በማሳካት በተማሪ የሚታየው ለውጥ በየጊዜው ይተነተናል እና ውይይት ይደረግበታል (የመነሻ አሃዝ በመቶኛ 60%)
- እና ለወላጆች፤
  - አስተማሪ እና ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሞያዎች (ቴራፒስት) ጭምር የእርሱ/እርሶ ልጆች ከፍ ያለ ዉጤት እንደሚያሳዩ እምነት ያደረባቸው ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ (መነሻው በመቶኛ 72% በአጠቃላይ )
  - የእርሱ/እርሶ ልጆች በትምህርት አጠቃላይ የአካዳሚ መሻሻል እርካታ (መነሻው በመቶኛ 61% በአጠቃላይ )

# መጠቃለያ

- ኤሲፒኤስ ወደፊት ለማደግ የሚያስችል አስተማማኝ መሰረት እንዳለው በቂ ማስረጃ አለ፡፡

- ነገር ግን  በዚህ ሪፖርት የተሰጡትን የመፍትሄ ሃሳቦች በትክክል በስራ ለማዋል የአጣዳፊነት ስሜት እና በትክክል የማያቋርጥ አትኩሮት ከሌለ የትምህርት ቤት አስተዳደሩ(ዲቪዥኑ) ቀጣይ ለውጥ አያሳይም፡፡

- ለውጥ ለማምጣት አትኮሮት፣  ከዋናው ሥራ አስኪያጅ(ሱፕር ኢንቴንደንት) የጠነከረ  እይታ እና በከፍተኛ የስራ ኋላፊዋች በተግባር ማዋልን፣ ተገቢ የሃብት ምደባ፣ የግዴታ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና  እና ግልጽ፣ ድርድር የሌለበት፣ የመላ ዲቪዝኑን ተጠያቂነት ያለው እርምጃዋችን ይጠይቃል፡፡

- የለውጥ ሂደት የእያንዳንዱን ሰራተኛ ተሳትፎ  እና ቁርጠኝነት እና የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዋች ከፍ ያለ ውጤት የመጠበቅን ፈቃደኝነት ይጠይቃል፡፡

ከዚህ የሚቀጥለው

# የቀጣይ እርምጃዋች ሂደት

- <u>ዓላማ፤</u> በዚህ ስራ በመላው ተቋም የግምገማው የመፍትሄ ሃሳብ እንዴት በስራ ለማዋል እንደሚቻል ከተለያየ መንገድ አንፃር የሚከናወኑ አቅጣጫ ለማስያዝ የውስጥና የውጭ ባለድርሻዋችን በማሰባሰብ የሦስት ዓመታት የተግባር እቅድ በማዘጋጀት ማቅረብ

- 36 የሚሆኑ የባለድርሻዋች የያዘ ቡድን ከእነዚህም ውስጥ 9 በዋና ኮሚቴ አባልነት የሚያገለግሉ ከጁን 2018 ጀምሮ  የተዘጋጀውን የረቂቅ የተግባር እቅድ በማሻሻል የቀረበውን የመፍትሄ ሃሳብ በስራ ለማዋል ኤሲፒኤስ ወደፊት እንዲራመድ ማድረግ

- ለዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐር ኢንቴንደንት) እና ለከፍተኛ የሥራ ኋላፊዋች ረቂቅ የተግባር እቅድ ማቅረብ

- የልዩነት(ጋፕ) ትንተና እና ግብረመልስ ለማከናወን ረቂቅ የተግባር እቅድ ለPCG መላክ

- የESB፣ ACPS *Express* እና  *ACPS Insider* መረጃ ማሳራጫዎችን በመጠቀም ሪፖርት ለሕዝብ ማሳወቅ

# ከዚህ በመቀጠል የጊዜ ቅደም ተከተል

**ኦክቶበር**

**25**

ሪፖርት ለቦርድ ማቅረብ

**ኖቬምበር**

**2**

ረቂቅ የተግባር ፕላን በESB ይወጣል

**ኖቬምበር**

**9-20**

የሕዝብ አስተያየት መጠይቅ እና ስብሰባዎች

**ዲሴምበር መጀመሪያ**

ሐኖቨር የሕዝብ አስተያየት ትንተና ያቀርባል

**ዲሴምበር**

**6**

ረቂቅ የተግባር ፕላን ለቦርድ ያሳውቃል

**ዲሴምበር አማካኝ**

ዋና ኮሚቴው የተግባር እቅድ ያጠናቅቃል።

**ዲሴምበር**

**20**

የመጨረሻ የተግባር እቅድ ለቦርድ ይቀርባል

**2019**

በስራ የዋለበት

1ኛ ዓመት

PUBLIC CONSULTING GROUP

www.publicconsultinggroup.com